# ለካስ ሲዋሸኝ ነው !!

(አሥራደው  ከፈረንሳይ)



ጭሰኝነት ቀርቶ - መሬት ላራሹ ነው፤
ከንግዲህ አበቃ - እርስቱ ያንተ ነው፤
ገባር እንዳትባል - ሙክት እንዳትጎትት፤
ቂቤ ማር እንዳትሰጥ - እንዳትከፍል አሥራት፤
ላንተ ስል ቆሜያለሁ - ስላንተ እሰዋለሁ፤
ይለኝ የነበረው - ለካስ ሲዋሸኝ ነው ።

ቃልኪዳን የገባው - የማለው መሃላ፤
ለካስ በእኔ ውርደት - ነው ሆዱን ሲሞላ ።

ክንዱን ከፍ አድርጎ - ይጮህ የነበረው፤
ጉሮሮው እስቲደርቅ - ቃላት ያዘነበው፤
መዝሙር የዘመረው- መፈክር ያቅራራው፤
በእኔ ስም ስለሙብት - ይሰብክ የነበረው፤
ላንተ ነው የቆምኩት ላንተ ነው እምሞተው፤
ይለኝ የነበረው፤
ለካስ ሲዋሸኝ ነው !
ለካሽ ሲሸጠኝ ነው !!

ቃልኪዳን የገባው - የማለው መሃላ፤
ለካስ በእኔ ውርደት - ነው ኪሱን ሲሞላ ።

በእኔ ስም ተዓለም ባንክ - ብድር ተበደረ፤
በእኔ ስም አብኩቶ - በኔ ስም ጋገረ፤
በእኔ ስም ወጥቆ - በእኔ ስም ወፈረ፤
መሬት ለአራሹ ነው ብሎ እንዳልፎከረ ።

ቃልኪዳን የገባው - የማለው መሃላ፤
ለካስ በእኔ ውርደት - ነው ሆዱን ሊሞላ ።

ቀፈፍኩት ለእይታ - ሳቀ በማጣቴ፤
እሱን እያስተማርኩ - አፈር በመግፋቴ፤
እሞታለሁ ላንተ - እሰዋለሁ ያለኝ ፤
ለካስ ሲዋሸኝ ነው - የቧሁን ሲያሞኘኝ፤
ለራስ መወጣጫ - መሰላል ሊያደርገኝ ።

ቃልኪዳን የገባው - የማለው መሃላ፤
ለካስ በእኔ ውርደት - ነው ኪሱን ሊሞላ ።

አንድ ቀን !

**ሞኝ ይስቃል - ብልህ ይጨነቃል !**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮን ሳይኖራት፤ በቀዳዳ ብቻ እያጮለቀ፤ ቀደም ብሎ ዘመነኞቹን፤ አሁን ደግሞ ተረኞቹን፤ ዓለማቸውን ሲቀጩ፤ በመመልከት ይኸው 30 ዓመታትን፤ አስቆጥሯል ።

አለመታደል ሆኖ፤ ዛሬም እንደገና፤ አብሮነታችን ቆዳቸውን የሚያሳከካቸው፤ ተረኛ ነን ባዮች የዘርና የጎሣ ፖለቲከኞች፤ በታጎሩበት የዘርና የጎሣ፤ በረት ( ክልል) ውስጥ ሆነው፤ ሻኛቸውን እያጎማለሉ ያገሱብናል ።

ሁላችንም እንደነሱ፤ ከአንድ ድንጋይ የተጠረብን ግዑዞች እንድንሆን ለሚዳዳቸው የዘርና የጎሣ ፖለቲከኞች የምንላቸው ቢኖር፤

እኛ: የአያትና የቅድም አያቶቻችንን ታሪክ፤ በፈረንጅ ላፒስ የምንፈገፍግ ነጭ አምላኪዎች ሳንሆን፤ በኢትዮጵያዊነት ማማችን ላይ ሆነን፤ በአብሮነታችን በመጽናት፤ **ዛሬን! በትምህርትና በሥራ መንገዳችን ነገን ! በአንድነት፤ በእኩልነትና በፍቅር ድልድያችን**: አድርገን፤ የወደፊቱን ተስፋ በአብሮነት ከአድማስ ባሻገር የምንቃኝ ኩሩ ዜጎች መሆናችንን ነው ።

የአስተሳሰብ ድንክዬዎች የሆኑት፤ የዘርና የጎሣ ፖለቲከኞች፤ « ዶሮ ብታልም ጥሬዋን እንዲሉ » ዘወትር ጠዋትና ማታ፤ የሚያላዝኑት ስለ፤ ክልል (መንደር) ፤ ጎሣ፤  ዘረኝነት ስርቆትና ጥላቻ ብቻ ነው ።

እነሱ ዛሬ ሲፈነድቁና ሲጨፍሩ፤ እኛ የነገው ለቅሶ ያሳስበናል። እነሱ ዛሬ ሲሰርቁና ሲዘርፉ፤ እኛ የነገው የአገራችን ዕዳ ያስጨንቀናል ። እነሱ ዛሬ ጥላቻና በቀል ሲሰብኩ፤ እኛ የወደፊቱ ፍቅርና ወንዳማማችነት መናድ ያሳስበናል። እነሱ ዛሬ ህፃናትን፤ እናቶችና አዛውንትን በሜጫና በጠመንጃ እየፈጁ፤ ሲፎክሩና ሲያቅራሩ፤ እኛ የነገውን መሸማቀቅ እያሰብን እናፍራለን። እነሱ ስለ ክልልና መንደር ሲሰብኩ፤ እኛ ስለወደፊቱ አገራዊ አንድነትና አብሮነት መናድ እንሰጋለን ።

እኛ እንደነሱ: በዘርና በጎሣ በረት ውስጥ ተከልለን (ታጥረን) የምናገሳ ኮርማዎች ሳንሆን፤ በኢትዮጵያዊነት ማማችን ላይ ሆነን: ስለ አብሮነት፤ ስለ ሠላም፤ አንድነት፤ ፍቅርና ወንድማማችነት አበክረን የምንመክርና የምናሳስብ ዜጎች ነን ።

የዛሬው: የዘረኞችና የጎሠኞች የዘር ማጥፋት ወንጀል፤ ነገ በቀልን እንዳይወልድ በእጅጉ ያሳስበናል ።

**ሞኝ ይስቃል - ብልህ ይጨነቃል !**

አይምሮ ያለው ያስብ - ጆሮ ያለው ይስማ፤

**በኢትዮጵያ ከአሁን በኋላ ከመሸ፤ ተመልሶ አይነጋም** !!

ለወገኖቼ በአደራ መልክ የማስተላልፈው መልክት ቢኖር፤

የኮረና ቫይረስና፤ የዘርና የጎሣን ፖለቲካ ሁለቱም ገዳዮችና አገር አጥፊዎች በመሆናቸው

ለኮረና ቫይረሱ የጤና ጭንብል፤ ለዘርና የጎሣው ፖለቲካ፤ የአንድነት ጭንብል፤ አጥልቃችሁ ሁለቱንም በጋራ ተከላከሉ እላለሁ ።

አበቃሁ !

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያናን ሕዝቧን ይባርክ !!!